# በሁሉም ክፍሎች ጥራት ያለው ትምህርት እንዲኖር ማድረግ

## አጭር መግለጫ

በክልላችን በሚገኙ ትምህርትቤቶች ሁሉ በእያንዳንዱ የመማሪያ ክፍል ውስጥ አስፈላጊውን ነገር ና ማቴሪያል የተሟላላቸው ክፍሎችና እንዲሁም ብቃትና ጥሩ ችሎታ ያላቸው አስተማሪዎችና ሌሎች ረዳት አስተማሪዎች እንዲኖሩ ማድረግ በጣም ወሳኝ ነው።

ተማሪዎች ትምህርታቸው ጨርሰው ለመመረቅና የወደፊት ህይወታቸው የተሳካ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችል በሁሉም ትምህርትቤት ደረጃውን የጠበቀ እኩል ስርአተ ትምህርት እንዲኖር ማድረግ በጣም ወሳኝ ነው። አስተማሪዎችና ረዳት አስተማሪዎች የተማሪዎች ችሎታና እድገት እና እንዲሁም የተማሪው ጠንካራ ና ደካማ ጎን የሚለኩበትና የሚከታተሉበት አሰራር እንዲኖር ማድረግ ወሳኝ ነው።በዚህ መልክ ተማሪው አስፈላጊውን ድጋፍና እርዳታ እንዲያገኙ ያደርገዋል ማለት ነው።

## ዋና አስፈላጊ ነገሮች

በዚሁ አመት ልዩ ትኩረት የሚሰጥባቸው የተለያዩ ነጥቦች ለመጠቀስ ይቻላል.

**የሂሳብና ሳይንስ ተስማሚ ስርአት ትምህርት መንደፍ** – ለስነ ጽሑፍ ልዩ ትኩረት በመስጠታችን ተማሪዎቻችን በጽሁፍና በንባብ በጣም ጥሩ ውጤት አስመዝግበዋል። አሁን ደግሞ ጥሩ ውጤት ለማምጣት በሂሳብና ሳይንስ ትምህርት ልዩ ትኩረት ለመስጠት እንፈልጋለን።በአሁኑ ሰአት በሂሳብና ሳይንስ ትምህርት ጥሩ ችሎቻ ያላቸው ተማሪዎች ቁጥር በጣም አንስተኛ ነው።ተማሪዎች በሂሳብና በሳይንስ ትምህርት ጥሩ ችሎታና እውቀት እንዲኖራቸው ማድረግ በጣም ወሳኝ ነው። የሂሳብና ሳይንስ ስርአተ ትምህርት ላይ ልዩ ትኩረት መስጠት ተማሪዎች ከትምህርትቤት ለመመረቅ የሚያስችላቸው ጥሩ እውቀትና ችሎታ እንዲኖራቸው ያደርጋል።ሁለቱም የትምህርት አይነቶች ስርአተ ትምህርቱ በማስማማት አስተማሪዎችና ትምህርትቤቶች አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያገኙ ለማድረግ ይረዳል።

**የተማሪዎች ደረጃ የሚገልጽ መረጃ ማዘጋጀት** – ተማሪዎች ጠንካራና ደካማ ጎናቸው ለይቶ ለማወቅና አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያገኙ ለማድረግ አስተማሪዎችና ረዳት አስተማሪዎች የሚጠቀሙበት የተማሪዎች ደረጃ የሚያሳይ ሙሉ መረጃ እንዲኖር ይፈለጋል። በዚህ መልክ አስተማሪዎች በይበልጥ ተማሪው አሳፈላጊውን ድጋፍና እርዳት ሊሰጡ ይችላሉ ማለት ነው።የዚሁ አይነት መረጃ ለአስተማሪዎችና ረዳት አስተማሪዎች እንዲኖር ለማድርግ ከአስተማሪዎችና ከርእሰ መምህራን ጋር በቅርብ ተባብረን እንሰራለን።

**የትምህርትቤቶች እድገት የሚለካበት አሰራር እንዲኖር ማድረግ** – በዚህ መልክ የእያንዳንዱ ትምህርትቤት የሚያስመዘግቡት የአካዳሚክ ውጤታቸው የሚለካበት አሰራር እንዲኖር በማድረግ ድክመት የሚያሱ ትምህርትቤቶች ካሉም በጊዜው አስፈላጊውን ድጋፍና እርዳታ እንዲያገኙ ማድረግ።ይህ አሰራር በዚሁ አመት ማለት በ2008 መጨረሻ አካባቢ ላይ እንዲነደፍ ይደረግና በ09-10 የትምህርት ዘመን ሙሉ በሙሉ ስራ ላይ እንዲውል ይደረጋል።

## ለህብረተሰቡ የሚቀርቡ ጥያቄዎች

- በይበልጥ ለማወቅ የምትፈልጉት ነገር ምንድነው?
- ግልጽ ያልሆነላችሁ ነገር ካለ?
- የጎደለ ነገር ካለ?
- ስለ አሰራራችን ያሉት መረጃዎች ሁሉ በምን መንገድ እንዲደርሳችሁ ትፈልጋላችሁ?